መንገሻ ዮሃንስ

አዲስ አበባ

**ውጉዝ ከመ አሪዮስ!**

የኤርትራ ህዝብ ከ30 ዓመታት መራራ የትጥቅ ትግል በውኋላ እ.ኤ.አ. 1991ዓ.ም. ነፃነቱን እንደተቀዳጀ ትንሽ ሳያርፍና ገና የሃገሪቱ ኢኮኖሚ እና ፖለቲካ ሁኔታዎች መሰረት ሳይዙ የኤርትራ መንግስት  ልክ እንዳበደ ውሻ ጐረቤቶቹን መናከስ ጀመረ። በዓለም ለነፃነት የተደረጉ ተጋድሎዎችን ስንመለከት አንግበዋቸው ከሚነሱት ዋና ዋና ዒላማዎች መካከል ዜጐች በነፃነት እንዲያስቡ፣ እንዲንቀሳቀሱ፣ እንዲፅፉ፣ የፈለጉትን ፖለቲካዊ አስተሳሰብ እንዲያራምዱ ፣ሀብት እንዲያፈሩና ባፈሩት ሃብት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና ባጠቃላይ በህ/ሰቡ ሁለንትናዊ ዕድገት ማምጣት ሲችሉ ነው ትግላቸው ተሳክቷል የሚባለው ። የኤርትራ ህዝብ የነፃነት ትግል ውጤት ግን የዚህ የተገላቢጦሽ መሆኑ ጎረቤት አገሮችን በመውረር ፣አሸባሪዎችን በማደራጀትና በማስታጠቅ አከባቢውን የማተራመስ አጀንዳ ይዞ ከሚንቀሳቀስ መንግስት የሚጠበቅ እንጂ አስገራሚ አይሆንም።

የኤርትራ መንግስት ጎረቤቶቹን ልክ እንደ ኮሻሽላ እሾህ መዋጋት የጀመረው ገና በነፃነት ማግስት እ.ኤ.አ ታህሣሥ 19 ቀን 1995 ዓ.ም የየመን ይዞታ የነበረችው የሓኒሽ ደሴት ይገባኛል በማለት ዘሎ በጉልበቱ በመውረር ነበር:: ጥቅምት 9 ቀን 1998 ዓ.ም በ**International** Arbitration **Panel** ደሴቷን የየመን እንደሆነች ስለተወሰነ ወራሪው የኤርትራ መንግሰት የብዙ ሂወትና ንብረት መጥፋት ምክንያት ከመሆን በዘለለ ለታገለለት ህዝብ ምንም ሳይፈይድ በሀፍረት ደሴቷን ለቆ ወጣ.። አገራችን ከኤርትራ መንግስት ጋር ብዙ ያልተፈቱ ችግሮች መኖራቸውን ብታውቅም ጉዳዩ በሰላምና በድርድር ይፈታል ብላ አምና የነበረውን ሰራዊት ትልቅ በሚባል መጠን ቀንሳ ወደ ልማት መግባቷ እና ይህንንም ተከትሎ በድንበሩ አካባቢ ምንም ዓይነት ወታደራዊ እንቅስቃሴ ያለመኖሩን እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም ግንቦት 1998 ዓ.ም የኢትዮጵያን ድንበር ወሮ ያዘ። በአፍሪካ ሕብረት፣በአውሮፓ ህብረትና በተባበሩት መነግስታት ችግሩ በሰላማዊ መንገድና በድርድር እንዲፈታ ቢጠይት አሻፈረኝ ብሎ የነበረው በጦርነቱ አሳፋሪ ሽንፈት ከገጠመው እና ከፍተኛ ለሆነ የሂወትና የንብረት ጥፋት ዳግም ምክንያት ከሆነ  በውኃላ ሳይወድ በግድ የአልጀርስ የሰላም ስምምነት መቀበሉን ገለፀ ይኸን ሁኔታ **BBC ማርች** 1, 1999"News of Ethiopia's victory declaration came hours after the United

Nations announced that Eritrean President Issaias Afeworki had accepted an Organisation of African Unity (OAU) peace plan which implies Eritrean withdrawal from the contested western Badme zone). "በማለት ገልየታል፡፡

በ2005 ዓ.ም በሙሳ አሕመድ የሚመራ ራሱን የምስራቅ ሱዳን ግንባር ብሎ የሚጠራ ተቃዋሚ የኤርትራ መንግስት እንደሚደግፍ እና በሱዳን መንግስት ሲከሰስ እንደነበረ"Although Darfur is some 1,000km away, Jem's headquarters are in Eritrea, which Sudan accuses of backing the eastern rebels)." በሚል BBC ሰኔ 23 ቀን 2005 ዓ.ም ያስነበበው መረጃ ያመለክታል ፡፡ በጣም የሚገርመው ነገር ደግሞ የዕብድ ገላጋይ እንዲሉ የኤርትራ መንግስት ልክ እንደ ሰላም ወዳድና የሱዳን ህዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል ራሱ የፈጠረውን ተቃዋሚ ከሱዳን መንግስት ጋር ጥቅምት 14 ቀን 2006 ዓ.ም አስመራ ላይ ልሽመግል ማለቱ የኤርትራ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ("Sudanese Government of National Unity and East Sudan Front sign Historic Peace Agreement in Asmara" በማለት መግለጫ መሰጠቱ ነበር፡፡

ሌላው ደግሞ በ2006 ዓ.ም የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድቤቶች ህብረት ኢትዮጵያ ላይ ጂሃድ ሲያውጅና በተባበሩ መንግስታት በአፍሪካ ህብረት እና በኢጋድ እውቅና የተሰጠውን የሶማሊያ ጊዚያዊ ፌደራላዊ የሽግግር መንግስት ለመጣል ህብረቱ ጦርነት ሲከፍት የኤርትራ መንግስት ከፍተኛ የመሪነት ሚና እንደነበረው የተባበሩት መንግስታት አጣሪ ቡድን ሐምሌ 28/2011 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ሪፖርት በ2006,ዓ.ም እና ከዛ በፊት የኤርትራ መንግስት የሶማሊያ ፌደራላዊ የሽግግር ምንግስት ተቃዋሚዎች ሲደግፍ እንደነበረ እና በሶማሊያ ሳይገደብ በጂቡቲ፣ኢትዮጵያ ፣ሱዳን እና ኡጋንዳ መሳሪያ ለታጠቁ ጠቃዋሚዎች በስልጠና፣በገንዘብ እና በሎጂስቲክስ መደገፉ የተባበሩት መንግስታት የመሳሪያ ክልከላ ማዕቀብ መጣሱን ያመለክታል በማለት ገልፆል፡፡ ህብረቱ ከተፈረካከሰ በውኃላም ቢሆን የኤርትራ መንግስት አከባቢውን ለማወክና የሽግግር መንግስቱን ለመጣል የሚዋጉትና ከዓለም አቀፉ አሸባሪ ድርጂት ከሆነዉ ዓልቃዒዳ ጋር ግንኙነት ያለውን ዓልሻባብ ፣ ARS(Alliance for the Re-Liberation of Somalia)እና Raas Kaambooni ሃይሎች በስልጠና ፣መሳሪያና ገንዘብ መስጠትን ጨምሮ ሁለንተናዊ ድጋፍ ሲሰጥ እንደነበረ የተባበሩት መንግስታት አጣሪ ቡድን ሐምሌ 28 ቀን 2011 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ሪፖርት በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 8 ቀን  2008 ዓ.ም ከግረቤቶቿ መልካም ግኑኝነት ያላት ጂቡቲን በዕብሪት መውረሩን The New York Times: ”The Djiboutian  say the Eritreans invaded in January and point to Eritrea's history of friction with just about all of its neighbors. They suggest that the country either thrive on war or has gone a little border-crazy. ” በማለት ግንቦት25 ቀን 2008 ዓ.ም አስነብቦአል፡፡

የትርምስ አባዜ የተጠናወተው የኤርትራ መንግስት የማተራመስ ፖሊሲዉን ከቀጠናችን አልፎ ህንድ ውቅያኖስን ተሻግሮ የሲሪላንካ ተቃዋሚ ለነበረው እና በ32 አገራት በአሸባሪነት የተፈረጀውን [Liberation Tigers of Tamil Eelam] የተሰኘ ቡድን አጅሬው ድጋፍ እየሰጠ ሲያተራምስ እንደነበረ **The Island newspaper** መስከረም 28/2009 ባወጣው እትሙ ገልፆዋል አያይዞም ([Liberation Tigers of Tamil Eelam] ከኤርትራ ምንግስት ጋር ጠንካራ ግንኑነት መፍጠሩንና ቡዱኑ የኤርትራ መንግስት end-user certificates በመጠቀም የጦር መሳሪያዎች፣የተለያዩ ጥይቶች እና የተለያዩ የጦር ቁሳቁሶች በህጋዊ መንገድ እየገዛ  ሲገለገል እንደነበር ገልፆዋል:: በተጨማሪ ይኽን ጉዳይ በተመለከተ **Asian Tribune** ዋቢ በማድረግ ሰፊ ተነባቢነት ያለውን Africapath የተሰኘ ድህረ-ገፅ መስከረም 2007 ዓ.ም እንደገለጸው የኤርትራ መንግስት ሪፖርት ለ LTTE ቀጥታዊ ድገፍ እንደሚያደርግ የሚያረጋግጥ ሲሆን ባጠቃላይ የሱዳን መንግስትን ለሚቃወሙ ታጣቂ ሚሊሻዎች ፣ለሶማሊያ አሸባሪ ቡድኖች፣ለጂቡቲ እና ኢትዮጵያ ፀረ-መንግስት ሀይሎች ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሰጥና ይህ ሁኔታ የኤርትራ መንግስት ምንያህል የአፍሪካ ቀንድ እያተራመሰ እንደሆነ ያሳያል በማለት ገልፆታል፡፡

የኤርትራ መንግስት ከሚመራበት የጫካ ፖለቲካ ወጥቶ ወደ ዘመናዊ የዲፕሎማሲ መፍትሄዎች እንዲመጣ በተለያዩ መንገዶች ሲጕተጉቱት የነበሩት የፀጥታው ምክር ቤት  አባል አገራት ከዚህ እኩይ ተግባሩ እንዲታቀብ  ታኅሳስ 23/2009 በኡጋንዳ አዘጋጅነት፣ በኢጋድና በአፍሪካ ኅብረት ድጋፍ አግኝቶ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በኤርትራ መንግስት  ላይ ማዕቀብ  በመጣል ለመጀመሪያ ጊዜ ለኤርትራ መንግስት ሲያራምደዉ ለነበረዉ የማሸበር ስትራቴጂ የዓለም ህብረተሰብ ድርጊቱን አወገዘ፡፡ ማዕቀቡ የመሳሪያ ዝውውር ክልከላ (Arms Embargo) የጉዞ ክልከላ (Travel bans) በመሪዎቿ እንዲሁም የሃብት ዝውውር ክልከላ (Asset freezing) እንደነበር ይታወሳል፡፡

ይህ ሁሉ የተደረገው የኤርትራ መንግሥት አደብ እንዲገዛና ከማተራመስ ተግባሩ እንዲታቀብ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ሻዕቢያ በባህሪው ከስህተቱ የሚታረም ስላልሆነ አከባቢውን የማተራመስ ስራውን አጠናክሮ በመቀጠል ጥር 2011 የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ በሚካሄድበት ቦታና ህዝብ በብዛት በሚንቀሳቀስባቸው የአዲስ አበባ አካባቢዎችን በቦምብ ለማጋየት ያልተሳካ ሙከራ ማድረጉ የተባበሩት መንግስታት አጣሪ ቡድን ሐምሌ 28 ቀን 2011 ዓ.ም ይፋ ባደረገው ሪፖርት "The report states that the Eritrean Government "conceived, planned, organized and directed a failed plot to disrupt the African Union summit in Addis Ababa by bombing a variety of civilian and governmental targets." የሺብር ቅንብሩን በቀጥታ በኤርትራ መንግስት ይመራ እንደነበረ በግልጽ አስታውቀዋል፡፡ ይህ ሴራ ባይከሽፍ ኖሮ ምን ያህል አሰቃቂ እልቂት ሊደርስ እንደነበር ለመገመት አይከብድም፡፡

የተባበሩት መንግሥታት አጣሪ ቡድን (UN Monitoring Group on Somalia and Eritrea) ሐምሌ 28/2011 ይፋ ካደረገው ሪፖርት በመነሳት የኢጋድ አባል አገራት ቀጠናውን በሚያተራምሰው የኤርትራ መንግስት ላይ ተጨማሪ ማዕቀብ እንዲጣል ያለ ልዩነት ጠየቁ፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታ ም/ቤትም ይህንን ሪፖርት ከመረመረና ካረጋገጠ በውኋላ በጋቦን እና ናይጄሪያ አቅራቢነት የቀረበውን ማዕቀብ ታህሣሥ 1/2011 በ13 ድጋፍ እና በሁለት ድምፀ-ተአቅቦ ማዕቀብ ቁጥር 2023 እንዲጣልበት የፀጥታው ም/ቤት ውሳኔ በማስተላለፍ የኤርትራ መንግስት አከባቢውን ለማተራመስ ለሚያራምደው ስትራቴጂ በድጋሜ አወገዘ፡፡

የውሳኔው ዋና ዋና ጪብጦች፡- ምክር ቤቱ ታህሣሥ 23 ቀን 2009 ዓ.ም ያስተላለፈውን ማዕቀብ ቁጥር 1907 ሙሉ በሙሉ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ የኤርትራ መንግስት በውጭ ከሚገኙ ኤርትራውያን ወርሃዊ ገቢያቸው 2% እያስገደደ የሚሰበስበውን ግብር በቀጥታ የኤርትራ መንግስት ለሚመራው ድርጂት_PFDJ (People's Front for Democracy *and_Justice*) እንዳይተላለፍና አካባቢውን ለማተራመስ፣ ተቃዋሚዎችን ለመደገፍና በአጠቃላይ የአካባቢውን ሰላም ለማደፍረስ ለሚያደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ እንዳይውል የሚመለከታቸዉ አካላት ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርጉ፣የኤርትራ መንግስት በውጭ ከሚገኙት ኤርትራውያን በማስፈራራት፣ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ፣ ስጋት በመፍጠር ወዘተ የመሳሰሉ ህገወጥ እንቅስቃሴዎችን በማካሄድ ከገቢያቸው 2% የሚሰበስበውን ግብር እንዲያቋርጥ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የተባበሩት መንግስታት አባል አገራት በቬና ስምምነቶች ማለትም 1961 እና

1963 የድፕሎማቲክ እና ኮንሱላር ግንኙነቶች መሰረት እርምጃ እንዲወስዱ እንዲሁም የኤርትራ መንግስት ከዳያስፖራ የሚሰበስበውን ቀረጥ በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸዉ አገራት በድንበር ፣ በባህር እና በአየር መንገዶቻቸው አማካኝነት የሚሰጡትን የወደብ አገልግሎቶች በቁሳዊ ይሁን በገንዘብ፣ በቀጥታም ሆነ በተዛዋዋሪ ለሽብር እንዳይውል ጥብቅ ቁጥጥርና ፍተሻ እንዲያደርጉ ያስገድዳል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የኤርትራ መንግስት በማዕድን ዘርፍ ሽያጭ የሚያገኘውን ገንዘብ ቀጠናውን ለማወክ እንዳያውለው ግልፅነትና ተጠያቂነት መሰረት አድርጉ ከተባበሩት መንግሥታት የቁጥጥር ቡድን ጋር እንዲተባበር እና አባል አገራቱ የኤርትራ መንግስት የማዕድን ዘርፉ ለሽብር እና ትርምስ ተግባራት እንዳያውለው በኢንሹራንስ፣በባንክ እና በሌሎች የገንዘብ ተቋሞቻቸው እንዲሁም በዜጎቻቸውና በሌሎች አካላት የሚደረገውን እንቅስቃሴ እና በተጨማሪም በማዕድን ዘርፉ የሚደረጉ አዳዲስ የኢንቨስተትመንት እንቅስቃሴዎች ጭምር ማንኛውንም ማዕቀብ የሚጥሱ እንዳይሆኑ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ያስገድዳል፡፡

ይህ ውሳኔ መተላለፍ የሚያሳየው የኤርትራ መንግሥት ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ይበልጥ እየተነጠለ መሄዱን ብቻ ሳይሆን በኢጋድ አባል አገራትና በአፍሪካ አህጉር ደረጃ የኤርትራ መንግሥት በያዘው የማተራመስ ስትራቴጂ ላይ ያላቸውን ጠንካራ ተቃውሞ በትክክል ያሳየም ጭምር ነው፡፡ ይህ ደግሞ የኤርትራ መንግስት ነጋ ጠባ በተለያዩ ባለስልጣናቱ አማካኝነት በአሜሪካ የተጠነሰሰ ሴራ ነው ብሎ በተለያዩ ሚዲያዎች እንደሚያናፍሰው ሳይሆን የራሱ ፀረ-ሰላም ፖሊሲ ያስከተለው ውጤት መሆኑ እና በዲፕሎማሲው ትግል የደረሰበትን ከፍተኛ ሽንፈት የሚያሳይ ነው፡፡

በመጨረሻም እነዚህ ተከታታይ ማዕቀቦች መጣላቸው የኤርትራ መንግስት በኤርትራ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና መከራም የአለም መንግስታት እንዲያውቁት እና ወደፊቱም ለመፍትሄው የራሳቸዉን ድርሻ እንዲወጡ ያደርጋቸዋል፡፡ እነዚህ ማዕቀቦች ለኤርትራ ህዝብ ያላቸውን ፋይዳ ስናይ ደግሞ የኤርትራ መንግስት ለሁለት ድፍን አስርት ዓመታት አከባቢውን ለማተራመስ የሚያውለውን የኤርትራ ዜጎችን ሂወትና ሀብት በልማትና የህዝቡን ኖሮ

ለማሻሻል ለሚረዱ ተግባራት እንዲያውለው የሚያስገድድ ውሳኔ ከመሆናቸዉም በላይ በየተኛውም መመዘኛ የኤርትራ ህዝብ የሚጎዳ አለመሆኑን ማየት ይቻላል ።